# የወንጀል ቅጣት አወሳሰን በሃረሪ ክልል

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች:-**

**ጋሻዬ መረሳ**

የባልና ሚስት መወራረስን በተመለከተ በእኩል ምናልባትም በህይወት ያለው ባል ወይም ሚስት የበለጠ የንብረት ወይም የሀብት ማፍራት ሂደት ውስጥ ተሳታፊ ሊሆን በሚችልበት ሁኔታ ውስጥ አትውረስ ማለትና በዚህ ሂደት ውስጥ ምንም ቀጥተኛ የኢኮኖሚያዊ አስተዋፅኦ የሌላቸውን ሰዎችና መንግስትን በቅድሚያ መጋበዝ በጣም ተገቢነት የሌለው ሥርዓት እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡ በሀገራችን ካለው ጥብቅ ቤተሰባዊና ማህበራዊ እሴቶቻችን በመነሳት የባልና የሚስት እርስ በእርስ የመወራረስ ጉዳይ የሚያጠያይቅ ጉዳይ አለመሆኑን ነው፡፡ ከዚያ ይልቅ በየትኛው የወራሽነት ደረጃ ላይ ይቀመጡ የሚለው ዋናው ጥያቄ መሆኑን በመረዳት ጉዳዩን ከአገሪቱ ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶችና ልማዶች በመመርኮዝና የተለያዩ አማራጮችን በመመልከት መወሰኑ አስፈላጊ ነው፡፡ ባልና ሚስት በጋራ ያፈሩትን ንብረት የሟች የውርስ ሀብት አድርጎ አንዱን በማግለል በጋራ ካፈሩት ንብረት እንዳይጠቀሙ ማድረግ ማህበራዊ ግምት ውስጥ ካለማስገባቱም በላይ ከቤተሰብ ሕጉ ጋር የሚጋጭ ነው፡፡

ወንጀሎችን ከቅጣት ደረጃ አንጻር ስንመለከት በሁሉም ወንጀሎች ከመመሪያው በፊት በአብዛኛው ቅጣቶች የሚወድቁት በዝቅተኛ ደረጃ ሲሆን ከመመሪያው በኋላም በተመሳሳይ መልኩ ታይቷል፡፡ ከመመሪያው በፊት ከ53 ጥፋተኞች በዝቅተኛ ደረጃ 33 (62.26%) በመካከለኛ ደረጃ 4 (7.54%)እና በከባድ ደረጃ 1 (1.88%)ተቀጥተዋል፡፡ከመመሪያው በኋላ ከ58 ተከሳሾች በዝቅተኛ ደረጃ 37 (63.76%) በመካከለኛ ደረጃ 4 (6.89%)በከባድ ደረጃ 2 (3.44%)በበጣም ከባድ 1 (1.72)ተወስኖባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ በዝቅተኛ ደረጃ የመቅጣት ሁኔታ ከመመሪያው በኋላ በ1.53% መጨመሩን መረዳት ይቻላል፡፡ ቢሆንም በዝቅተኛ ቅጣት የማተኮር ሁኔታ በስርቆት እና በቸልተኝነት ሰው መግደል እና አስገድዶ መደፈር ወንጀሎች ሲቀንስ በቀሪዎቹ ጨምሮ ታይቷል፡፡ በአስገድዶ መድፈር ወንጀል በከባድና ከዛያ በላይ ደረጃዎች የሚቀጡ ጥፋተኞች የመጨመር ሁኔታ አሳይቷል፡፡ ነገር ግን በሁሉም ወንጀሎች ከህጉ ጣሪያ በላይ የተወሰነበት ጥፋትኛ የለም፡፡ ( ሰንጠረዥ 4 እና 5ን ይመልከቱ)

የአማካይ የእስር ጊዜን በተመለከተ ደግሞ በስርቆት እና በውምብድና ወንጀሎች ጨምሯል፡፡ በሙስና እና በአስገድዶ መድፈር ወንጀሎች ሲቀንስ በቸልተኝነት ሰው መግደል ለውጥ አልታየም፡፡ በአጠቃላይ ስናየው ከመመሪያው በፊት 3 አመት ከ5 ወር ከ7 ቀን የነበረው አማካይ የእስር ጊዜ ከመመሪያው በኋላ 3 አመት ከ5 ወር ከ7 ቀን ከ9 ሰዓት ነው፡፡ ከመመሪያው መውጣት በኋላ በ0.11% ቢጨምርም ምንም የጎላ ልዩነት አላሳየም ማለት ይቻላል፡፡